


በፕሬዘደንት ቶማስ ኤስ ሞንሰን

# በረከቶችን አስቡባቸው

*የሰማይ አባታችን ምን እንደምንፈልግ ያውቃል እናም እርሱን ስንጠራ እርዳታ ይሰጠናል።*

ውድ ወንድሞቼና እህቶቼ፣ በጥቅምት 4፣ 1963 (እ.ኤ.አ) እንደ አስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን አባል አንዱ የመሆን ድጋፍ ከተሰጠኝ ይህ ጉባኤ 49ኛው አመት ነው። አርባ ዘጠኝ አመት ረጅም ጊዜ ነው። በብዙ መንገዶች ግን ለመጀመሪያ ጊዜ በአጠቃላይ ጉባኤ ተነስቼ የመጀመሪያ ንግግርን የሰጠሁበት ግን ብዙ ጊዜ ያለፈበት አይመስልም።

ከጥቅምት 4፣ 1963 (እ.ኤ.አ) በኋላ ብዙ ነገሮች ተቀይረዋል። በአለም ታሪክ ውስጥ ልዩ በሆነ ጊዜ ነው የምንኖረው። በብዛት ተባርከናል። ግን በአካባቢያችን ያለውን ችግሮችና ኃጢያትን ለመቀበል ፈቃደኝነት ያለውን በመመልከት ተስፋ ላለመቁረጥ ያስቸግራል። በመጥፎው ላይ በማተኮር ሳይሆን በህይወታችን ያለውን በረከቶች ብንመለከት ታላቅ ደስታ እናገኛለን።

ያለፉትን 49 አመታት ሳስብባቸው፣ አንዳንድ ነገሮችን አግኝቻለሁ። ከእነዚያም አንዱ ከቁጥር በላይ የሆኑ አጋጣሚዎች የነበሩኝ ከሁሉም በላይ የሚደንቁ አልነበሩም።በእርግጥም፣ በሚደርሱበት ጊዜ በአብዛኛው ጊዜ የማያስደንቁና ተራ የሆኑ ይመስሉ ነበር። ነገር ግን በኋላ ሳስብባቸው፣ የእኔን ብቻ ሳይሆን፣ ህይወቶችን አበልፅገዋል እናም ባርከዋል። እናንተም ስለህይወታችሁ በጥንቃቄ እንድታስቡባቸው እና ትልቅም ይሁኑ ትንሽ ለተቀበላችኋቸው በረከቶች እንድትመለከቱ አበረታታችኋለሁ።

ባለፉት አመታት የነበሩትን ሳስብባቸው፣ ጸሎታችን እንደሚሰሙና መልስ እንደሚያገኙ ያለኝን እውቀት አጠናክረውልኛል። በመፅሐፈ ሞርሞን በ2ኛ ኔፊ ውስጥ “ሰዎች የሚኖሩትም ደስታም እንዲኖራቸው ዘንድ ነው”[1] የሚል እውነት እንዳለ እናውቃለን። አብዛኛው ያ ደስታ የሚመጣው ከሰማይ አባታችን ጋር በጸሎት ለመነጋገር እና እነዚያም ጸሎቶች እንደሚሰሙና መልስ እንደሚያገኙ በማወቅ ነው፣ ምናልባት ይመለሳሉ ብለን በማናስበብት ሁኔታ ቢመጡም፣ በፍጹምነት በሚያፈቅረንና በሚያውቀን እና ደስታችንን በሚፈልግ የሰማይ አባት ይመለሳሉ። እርሱም “ትሁት ሁን፤ እና ጌታ አምላክህ እጅህን ይዞ ይመራሀል፣ እና ለጸሎቶችህም መልስ ይሰጥሀል”[2] ብሎ ቃል ገብቶልናል።

ለተሰጠኝ ለሚቀጥሉት ትንሽ ደቂቃዎች፣ ጸሎቶች ተሰምተው፣ በኋላም ሲታሰብበት ለህይወቴ እና ለሌሎች በረከቶች ያመጡ መልሶች እንዴት እንደተሰጡ የነበሩኝን አጋጣሚዎች ለመካፈል እፈልጋለሁ። በየቀኑ የምጽፋቸው ማስታወሻዎች በሌላ መንገድ ለማስታወስ የማልችላቸውን ነገሮች እንዳስታውስ ረድቶኛል።

በ1965 (እ.ኤ.አ) የካስማ ጉባኤን እንድሳተፍበትና በደቡብ ፓስፊክ አካባቢ ስብሰባዎችን እንድሳተፍባቸው ተመድቤ ነበር። ይህን አካባቢ የጎበኘሁት ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር፣ እናም ይህም የማይረሳ ጊዜ ነበር። አብዛኛው አጋጣሚዎች ከመሪዎች፣ ከአባላት፣ እና ከወንጌል ሰባኪዎች ጋር ስገናኝ የነበሩኝ መንፈሳዊ ነገሮች ነበር።

በየካቲት 20ና 21 ቅዳሜና እሁድ፣ በብሪዝብን ካስማ ጉባኤ ለመሳተፍ በብሪዝብን አውስትሬሊያ ነበርን። በቅዳሜው ስብሰባ፣ በሚቀጥለው አካባቢ የነበረ ዲስትሪክት ፕሬዘደንት ጋር ሰዎች አስተዋወቁኝ። ከእርሱ ጋር ስንጨባበጥ፣ ከእርሱ ጋር መነጋገርና እርሱንም መምከር እንደሚያስፈልገኝ ስሜት ተሰማኝ፣ ስለዚህ ይህን ለማከናወን በሚቀጥለው ቀን ለእሁድ ስብሰባ ከእኔ ጋር እንዲመጣ ጠየቅሁት።

ከእሁድ ስብሰባ በኋላ፣ ለመነጋገር እድል ነበረን።፡እንደ ዲስትሪክት ፕሬዘደንት ስላለው ብዙ ሀላፊነቶች ተነጋገርን። ይህን ስናደርግ፣ ስለወንጌል መስበኪያ ስራ እና የሙሉ ጊዜ ወንጌል ሰባኪዎች በአካባቢው ሲያገለግሉ እርሱና አባላቱ እንዴት ለመርዳት እንደሚችሉ ልዩ የሆነ ሀሳቦች እንዳቀርብለት ተሰማኝ። በኋላም ስለዚህ ጉዳይ ያ ሰው እየጸለየ እንደነበረ አወቅሁኝ። ለእርሱም፣ ያ ንግግራችን ጸሎቱ እንደተሰሙና መልስ እንደተሰጣቸው የሚያውቅበት ልዩ ምስክር ነበር። ይህ አስደናቂ ያልሆነ ግንኙነት ነበር ግን ይህም በመንፈስ የተመራና በእዚያ ዲስትሪክት ፕሬዘደንት ህይወትና አመራር፣ በአባላቱ ህይወቶች ውስጥ፣ እና በዚያ ለነበሩት ወንጌል ሰባኪዎች ውጤታማነት ለውጥ ያመጣ ነበር።

ወንድሞቼና እህቶቼ፣ የጌታ አላማ የሚከናወነው እኛ የመንፈስን አመራር ስናዳምጥ ነው። በምንነሳሳበትና በሚሰማን ስንሰራ፣ ጌታ ተጨማሪ ስራዎቹን እንድናከናውን እምነቱን ይሰጠናል።

ባለፈው መልእክቶች እንደጠቀስኳቸው የመንፈስ መነሳሻን ለኋላ አታስቀምጡ። ከብዙ አመቶች በፊት አንድ ቀን እየዋኘሁ እያለሁ፣ በካንሰር እና በቀዶ ጥገና ምክንያት እግሮቹን መጠቀም የማይችለውን ጥሩ ጓደኛዬን በዩንቨርስቲ ሆስፒታል ሄጄ እንድጎበኝ መነሳሻ ተሰማኝ።ወዲያም ከመዋኛው ወጣሁ፣ ለበስኩኝ፣ እናም እርሱን ለመጎብኘት ወዲያው ሄድኩኝ።

በክፍሉ ስገባ፣ ማንም በክፍሉ እንደሌለ አየሁ። ስጠይቅም ለመንቀሳቀስ በሚሄድበው በሆስፒታሉ መዋኛ ቦታ ይገኝ እንደሚሆን ሰማሁ። ይህም ነበር። እራሱን በሚቀመጥበት ጋሪ ገፍቶ በክፍሉ የነበረ ብጨኛ ተጠቃሚ ነበር። በመዋኛው ቦታም በሚርቀ ክፍል ነበር።

ሰላም አልኩት እና እርሱም ወደ እኔ መጣ። በደንብ ተነጋገርን፣ እናም ወደ ሆስፒታል ክፍሉ ሄደን በረከት ሰጠሁት።

በኋላም ጓደኛዬ በዚያ ቀን ተስፋ ቆርጦ ህይወቱን ለመውሰድ ያሰብበት እንደነበረ አወቅሁኝ። ማረፊያ እንዲሰጠው ጸልዮ ነበር ግን ጸሎቶቹ መልስ የማያገኙ መስሎት ነበር። የሚቀመጥበትን ጋሪ ወደ ውሀው ጥልቅ ቦታ በመውሰድ ችግሩን የሚያፈጽምበት መንገድ እንደሆነ አስቦበት ነበር ወደ መዋኛ ቦታው የገባው። እዚያም የደረስኩት ከሰማይ የመጣ መነሳሻ ለሆነው በማውቀው መልስ በመስጠት አስፈላጊ በሆነው ጊዜ ነበር የደረስኩት።

ጓደኛዬ ለብዙ አመቶች ለመኖር ቻለ፣ እነዚህም በደስታና በምስጋና የተሞሉ አመቶች ነበሩ። በዚያ አስፈላጊ ቀን በመዋኛ ቦታ ላይ በጌታ እጅ መሳሪያ ለመሆን በመቻሌ ደስተኛ ነኝ።

አንድ ጊዜ፣ ጓደኞችን ከጎበኘን በኋላ እህት ሞንሰን እና እኔ ወደቤት እየነዳን እያለን፣ አንድ ጊዜ በዎርዳችን ይኖሩ የነበሩትን ባለቤ ታቸው የሞቱባቸውን ሴት ለመጎብኘት ስሜት መጣብኝ።ስማቸው ዜላ ቶማስ ነበር። እንክብ ካቤ በሚያገኙበት ቦታ ነበር የሚኖሩት። በዚያ ቀን በጣም ቢደክሙም በመኝታቸው ላይ በሰላም አርፈው ነበር።

ዜላ አይነ ስውር ነበሩ፣ ነገር ግን ድምጻችንን መጺያው አወቁት። ጌታ ወደ ቤት ለመመለስ የሚፈልጋቸው ከሆነ ለመሞት እንደተዘጋጁ በመናገር፣ በረከት እንድሰጣቸው ጠየቁኝ። በክፍሉም አስደሳችና ሰላም የሆነ መንፈስ ነበር፣ እናም ሁላችንም በስጋ የነበራቸው ጊዜ አጭር እንደነበረ አወቅን። ዜላ እጄን ያዙ እና እኔ እንድመጣና በረከት እንድሰጣቸው በሀይል ይጸልዩ እንደነበሩ ነገሩኝ። ከሰማይ አባት በተሰጠን ቀጥተኛ ምሪት ምክንያት እንደመጣን ነገርኳቸው። ምናልባት ወደፊት በሀይወት እንደገና ላላያቸው እንደማይሆን በማወቅ፣ ራሳቸውን ሳምኩኝ። ይህም እውነት ሆነ፣ ምክንያቱም በሚቀጠለው ቀን ሞቱ። ወደ ተወዳጇ ዜላ መፅናኛና ሰላም ለመስጠት መቻሌ ለእርሳቸው እና ለእኔ በረከት ነበር።

የሌላን ሰው ህይወት ለመባረክ ያለው እድል በማይጠበቅበት ጊዜ ነው የሚመጣው። በ1943–84 (እ.ኤ.አ) አንድ በጣም ብርድ በሆነ የቅዳሜ ምሽት፣ ሚድዌይ በሚባለው በዩታ ከተማ ወዳለን ቤት እህት ሞንሰን እና እኔ እየነዳን ነበር። በዚያ ጊዜ መጠነሙቀቱ ከዜሮ በታች 31 ድግሪ ሴልሲየስ ነበር፣ እናም በቤታችን ሁሉም መልካም እንደሆነ ለማወቅ ፈልገን ነበር። ሁሉንም ተመለከትን እና መልካም እንደሆነ ካየን በኋላ ወደ ሶልት ሌክ ለመመለስ መሄድ ጀመርን። በመንገዱ ለትንሽ ጊዜ ከተጓዝን በኋላ መኪናው መስራት አቆመ። በዚያ ምሽት እንደበረደኝ ከዚህ በፊት በርዶኝ አያውቅም ነበር።

ወደሚቀጥለው ከተማ መኪናዎች በፍጥነት ያለፉን በእግር መሄድ ጀመርን። በመጨረ ሻም አንድ መኪና ቆመልንና አንድ ወጣት እርዳታን አቀረበልን። በብርዱ ምክንያት በመኪናችን ውስጥ የነበረው ጋዝ ወፍሮ ነበር። በምድዌይ ወዳለው ቤታችን ሰውየው ነድቶ ወሰደን። ለሰጠን እርዳታ ልከፍለው ብሞክርም እምቢ አለኝ። እርሱ የቦይ ስካውት እንደሆንና ጥሩ ነገር ለማድረግ እንደፈለገ ነገረን። ማን እንደሆንኩኝ ነገርኩት እናም እርሱም እርዳታ ለመስጠት እድል ስላገኘ ምስጋናውን አቀረበ። ወደ ወንጌል ለማገልገል የሚሄድበት እድሜ ላይ የደረሰ ስለመሰለኝ፣ በወንጌል ሰባኪነት ለማገልገል አላማ እንዳለው ጠየቅሁት። ምን ማድረግ እንደሚፈልግ ለማወቅ እርግጠኛ እንዳልሆነ ነገረን።

በሚቀጥለው ሰኞ ጠዋት ለዚህ ወጣት ሰው ደብዳቤ ጻፍኩለትና ለደግነቱ አመሰገንኩት። በሙሉ ጊዜ በወንጌል ሰባኪነት እንዲያገለግል አበረታታሁት። ከጻፍኳቸው አንዱን መጽሀፍ አስገባሁና ስለወንጌል ሰባኪነት የሚናገረውን ምዕራፎች አሰመርኩባቸው።

ከሳምንት በኋላ እናቱ ደወለችልኝና ልጇ ጥሩ ልጅ እንደሆነ ግን በጓደኞቹ ምክንያት በወንጌል ሰባኪነት የማገልገል ፍላጎቱ እየቀነሰ እንደመጣ ነገረችኝ። እርሷና አባቱ ልቡ እንዲቀየር ሲጸልዩ እንደነበረ አመለከተች። ስሙንም በፕሮቮ ቤተመቅደስ የጸሎት ዝርዝር ውስጥ አስገብተውም ነበር። በአንድ መንገድ ልቡ በመልካም እንዲነካና የሙሉ ጊዜ ወንጌል ሰባኪ ለመሆንና ጌታን በታማኝነት ለማገ ልገል ያለው ፍላጎት እንዲመለስለት ተስፋ ነበራቸው። በዚያ ብርድ ጠዋት የደረሰውን ነገር ለእርሱ የጸለዩበትን መልስ እንደተሰጠ እንደምትመለከተውም ነገረችኝ።

ከብዙ ወሮች እና ከወጣቱ ጋር ለብዙ ጊዜ ከተነጋገርን በኋላ፣ እህት ሞንሰንና እኔ ወደ ብሪቲሽ ኮሎምቢያ ቫንኩበር የወንጌል መስ በኪያ ቦታ ከመሄዱ በፊት ለነበረው የወንጌል ሰባኪ ንግግር ላይ ለመገኘት በመቻላችን በጣም ተደሰተን ነበር።

በዚያ በታህሳስ ምሽት መንገዳችን የተተ ላለፈበት ምክንያት በእድል ነውን? እንዲህ እንደሆነ አላምንም። የተገናኘነው አባትና እናት ከልብ ለሚወዱት ልጅ ለጸለዩት መልስ እንደሆነ አምናለሁ።

እንደገናም፣ ወንድሞቼና እህቶቼ፣ የሰ ማይ አባታችን ምን እንደምንፈልግ ያውቃል እናም እርሱን ስንጠራ እርዳታ ይሰጠናል። የሚያሳስቡን ነገሮች በጣምም ትንሽ ናቸው ብዬ አላምንም። ጌታ በህይወታችን ድርጊቶች በሙሉ የሚያስብ ነው።

በብዙ መቶዎች የሆኑትን ስለነካው በቅርብ ስለነበረኝ አጋጣሚ በመናገር ንግግሬን ለመፈ ጸም እሞክራለሁ። የነበረውም ከአምስት ወር በፊት በካንሳስ ከተማ ቤተመቅደስ ባህል ማክ በሪያ ቀን ነበር። በህይወታችን እንደሚደርሱት ሌሎች ነገሮች አይነት፣ ይህም ሁሉም ነገር መልካም የሆነበት ሌላ አጋጣሚ መስሎ ነበር። ነገር ግን፣ ቤተመቅደሱ ከመባረኩ በፊት ከነበረው የባህል ማክበሪያ ድርጊቶች ጋር ምን አይነት ግንኙነት እንደነበረው ሳውቅ፣ የዚያ ምሽት ድርጊት ልዩ እንደሆነ ገባኝ። በጣም የሚያስደንቅም ነበር።

ቤተመቅደስን ከመቀደስ ጋር በባህል ማክበሪያ ሁሉ እንደሚደረገው፣ የካንሳስ ከተማ ምዙሪ የቤተመቅደስ አውራጃ ወጣቶች በተለያዩ ቦታ የእራሳቸውን ክፍል ተለማምደው ነበር። ሀሳባቸውም የባህል ማክበር በነበረበት በዚያ ቅዳሜ ጠዋት ተገናኝተው ምን ማድረግ፣ የት መቆም፣ በመካከላቸው ስንት ቦታ መኖር እንዳለበት፣ ከአዳራሹ እንዴት መውጣት እንደሚገባቸውና ሌሎችን በመለማመድ በዚህ ሀላፊነት ያላቸው የተለያዩ ድርጊቶችን አቀናጅ ተው የመጨረሻው ድርጊት በደንብ የተዘጋጀ እንዲሆን ከማድረግ እንዲቻላቸው ነበር።

በዚያ ቀን አንድ ብቻ ችግር ነበር። የሚደረ ገው በሙሉ በትልቅ ቲቪ እንዲታይ የተቀረጸ ነገር ላይ የሚመካ ነበር። እነዚህ የተቀረሱ ነገሮች ለማክበሪያው ድርጊት በጣም አስፈላጊ ነበሩ። ይህም ሁሉንም ነገሮች አንድ ላይ የሚ ያገናኝ ብቻ ሳይሆን፣ በቴሌቪዥን የሚታዩት ነገሮች ቀጥለው የሚመጡትን ድርጊቶች ያስ ተዋውቅ ነበር። በቪድዮ የሚታዩት የማክበር ድርጊቶች በሙሉ የሚመኩበት ነበር። ነገር ግን ትልቁ ቴሌቪዥን አይሰራም ነበር።

ወጣቶቹ የሚለማመዱባቸውን ጊዜ እያጡ፣ ሙያተኛ ሰዎች ለችግሩ መፍትሄ ለማግኘት በጣም ሞከሩ። ሁኔታው የሚቻል ያልሆነ መምሰል ጀመረ።

ጸሀፊና መሪ የነበረቻው ሱዛን ኩፐር ስንዲህ ገለጸች፣ "አላማችንን ስንቀያይር፣ የማይሰራ እንደሆነ አውቀን ነበር።. . . መርሀ ግብሩን ስንመለከት፣ ከምንችለው በላይ እንደሆነ አወቅን፣ ነገር ግን ከበታች ከሁሉም በላይ ጥንካሬአችን የሆነ ነገር እንዳለ አወቅን፣ ይህም 3 ሺህ ወጣቶች ነበሩ። ወደታች ወርደን ምን እንደደረሰ እነርሱን መንገርና እምነታቸውን መሳብ አስፈለገን።"[3]

ወደ መሰብሰቢያው ሰዎች ለመምጣት ከመጀመራቸው ከአንድ ሰዓት በፊት፣ 3 ሺህ ወጣቶች ተንበርክከው አብረው ጸለዩ። በትልቁ ቲቪ ላይ የሚሰሩት ይህን ለመጠገን ምን ማድ ረግ እንደሚያስፈልጋቸው እንዲያውቁ መነ ሳሻ እንዲኖራቸው ጸለዩ፤ አጭር መለማመጃ ጊዜ ስለነበራቸው፣ የሰማይ አባታቸውንም

እነርሱ እራሳቸው ለማድረግ የማይችሉትን እንዲያደርግላቸው ጠየቁ።

ስለዚህ ድርጊት የጻፈ አንድ ሰውም እንዲህ አል፣ "ወጣቶቹ ሊረሱት የማይችሉት ጸሎት ነበር፣ ይህም መሬቱ ጠንካራ ስለሆነ ሳይሆን መንፈስ በጣም ተሰምቷቸው ስለነበር ነውና።"[4]

ችግሩ ምን እንደሆነ እንደታወቀ እንደተ ጠገነ አንዱ ሞያተኛ መጥቶ የነገራቸው ከብዙ ጊዜ በኋላም አልነበረም። መፍትሄው የተገ ኘው "በእድል" ነበር አለ፣ ነገር ግን እነዚያ ወጣቶች በሙሉ ምን እንደነበር ያውቁ ነበር።

በአዳራሹ ውስጥ ስንገባ፣ የቀኑ ችግር ምን እንደነበር አላወቅንም ነበር። ያወቅነውም በኋላ ነበር። የተመሰከርነው ግን ካየኋቸው ሁሉ በላይ መልካም የነበረ በደንብ የተዘጋጀ ድርጊት ነበር። ወጣቶችም በዚያ የነበሩት ሁሉ የተሰማ ቸው አስገራሚና ሀይለኛ መንፈስ ነበራቸው። የት መግባት እንደነበረባቸው፣ የት መቆም፣ እና ከሌሎች ጋር እንዴት መስራት እንደሚገ ባቸው አውቀው ነበር። የተለማመዱበት ጊዜ አጭር እንደነበረ እና አብዛኛዎቹ የቀረቡት ድርጊቱን የተለማመዱ እንዳልነበሩ ሳውቅ፣ በጣም ተደንቄ ነበር። ይህን ማንም ሊያውቀው የማይችል ነበር። ጌታም እነርሱ ለማድረግ ያልቻሉትን አድርጓልና።

ጌታ መንግስቱን በሙሉ ለማነሳሳትና ለመምራት እየቻለ፣ ስለአንድ ሰው፣ ወይም አንድ የባህል መከበሪያን ወይም አንድ ትልቅ ቲቪን፣ በተመለከተ ምሪት ስለሚሰጥበት መገረሜን አላቆምም። ይህን ማድረግ መቻሉ ለእኔ ምስክርነት ነው።

ወንድሞቼና እህቶቼ፣ ጌታ በህይወታችን በሙሉ ውስጥ አለ። ያፈቅረናል። ሊባርከን ይፈልጋል። የእርሱን እርዳታ እንድንፈልግ ይፈልጋል። እርሱም ይመራናል፣ እናም ጸሎ ታችንን ሲሰማና መልስ ሲሰጥ፣ እርሱ በዚህና አሁን የሚፈልግልንን ደስታ እናገኛለን። በህይወታችን ውስጥ የሚገኙትን በረከቶች እንድናውቅ የምጸልየው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው፣ አሜን።

ማስታወሻዎች

1. 2 ኔፊ 2፥25።
2. ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች112፥10።
3. Susan Cooper, in Maurine Proctor, "Nothing's Too Hard for the Lord: The Kansas City Cultural Celebration," *Meridian Magazine*, May 9, 2012, ldsmag.com.
4. Proctor, *Meridian Magazine*, May 9, 2012.

# ለጊዜአችን ትምህርቶች

የመልከጸዴቅ ክህነትና የሴቶች መረዳጃ ማህበር የአራተኛው እሁዶች ትምህርቶች "ለጊዜአ ችን ትምህርቶች" የተወከሉ ይሆናሉ። እያንዳንድ ትምህርትም በቅርብ ከነበረው የአጠቃላይ ጉባኤ አንድ ወይም ተጨማሪ ንግግሮች መምረጥ ይቻላል። የካስማ እና የዲስትሪክት ፕሬዘደንቶች የትኛዎቹ ንግግሮች መጠቀም እንደሚገባቸው መምረጥ ይችላሉ፣ ወይም ይህን ሀላፊነት ለኤጲስ ቆጶስ እና ለቅርንጫፍ ፕሬዘደን ቶች ለመስጠት ይችላሉ። የመልከጼደቅ የክህነት ስልጣን ወንድሞች እና የሴቶች መረዳጃ ማህበር እህቶች አንድ አይነት ንግግሮችን በአንድ እሁድ ቀን ማጥናታ ቸው አስፈላጊነትን መሪዎች ደጋግመው ማሳሰብ ይገባቸዋል።

በአራተኛው ሰንበት ትምህርት ተሳታፊ ዎች የቅርቡን የአጠቃላይ ጉባኤ ጋዜጣን እንዲያጠኑ እና ወደ ክፍል እንዲያመጡ ይበረታቱ።

**ከእነዚህ ንግግሮች ትምህርትን የማዘጋጃ ሀሳቦች**

ንግግሮችን ስታጠኑ እና ስታስተምሩ መንፈስ ቅዱስ ከእናንተ ጋር እንዲሆን ጸልዩ። ሌሎች መፅሀፎችን በመጠቀም ትምህርትን ለማዘጋጀት ሀሳብ ይመጣላ ችሁ ይሆናል፣ ነገር ግን የጉባኤ ንግግሮች የትምህርት መረጃ እንዲሆን ፈቃድ የተሰጠበት ነው። የተመደባችሁትም በቤተክርስትያኗ የቅርብ አጠቃላይ ጉባኤ ውስጥ እንደሚገኙት ሌሎችን ወንጌሉን ለመኖር እና ለመማር እንድትረ ዱአቸው ነው።

የክፍል አባሎች ፍላጎትን የሚያሟሉ መሰረታዊ መርሆችን እና ትምህርቶችን በመፈለግ ንግግሮችን አጥኑ። ደግሞም ታሪኮችን፣ ቅዱስ መጻህፍት የተጠቀሱበ ትን፣ እና እነዚህን እውነቶች ለማስተማር የሚረዷችሁን ቃላቶች ፈልጉ።


መሰረታዊ መርሆችን እና ትምህርቶችን እንዴት እንደምታስተምሩም ዘርዝራችሁ ጻፉ። የክፍል አባላትን የሚረጡ ጥያቄዎ ችን አስቡባቸው።

- በንግግሮች ውስጥ መሰረታዊ መርሆችን እና ትምህርቶችን ፈልጉ።
- ስለትርጉማቸው አስቡበት።
- የተረዱትን፣ ሀሳባቸውን፣ አጋጣሚያ ቸውን፣ እና ምስክሮችን ይካፈሉ።
- እነዚህን መሰረታዊ መርሆች እና ትምህርቶች በህይወታቸው ይጠቀሙባቸው።

| ትምህርቶቹ የሚማሩበት ወራት | የአራተኛው እሁድ የትምህርት ማስረጃዎች |
|---|---|
| ጥቅምት 2012 (እ.ኤ.አ)–ሚያዝያ 2013 (እ.ኤ.አ) | በጥቅምት 2012 (እ.ኤ.አ) አጠቃላይ ጉባኤ የተሰጠ ንግግር* |
| ሚያዝያ 2012 (እ.ኤ.አ)–ጥቅምት 2012 (እ.ኤ.አ) | በሚያዝያ 2013 (እ.ኤ.አ) አጠቃላይ ጉባኤ የተሰጠ ንግግር* |

** ለሚያዝያ እና ለጥቅምት የአራተኛ ሰንበት ትምህርቶች፣ ወደፊት ከነበሩት ወይም በቅርብ ከነበሩት የጉባኤ ንግግሮች መምረጥ ይቻላል። እነዚህ ንግግሮች (በብዙ ቋንቋዎች) በ conference.lds.org ውስጥ ይገኛሉ።*

© 2012 በIntellectual Reserve, Inc መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩ.ኤስ.ኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፣ 6/11 (እ.ኤ.አ) ትርጉም የተፈቀደበት፣ 6/11 (እ.ኤ.አ) *First Presidency Message, November* 2012 (እ.ኤ.አ) *ትርጉም*። Amharic።10371 506



**በፕሬዘደንት ዲየትር ኤፍ. ኡክዶርፍ**

*የቀዳሚ አመራር ሁለተኛ አማካሪ*

# ስለጸጸቶች እና ውሳኔዎች

***ይህን መዝገብ አጥኑ እና ተገቢ ከሆነ ከምትጎበኟቸው እህቶች ጋር ተወያዩት። እህቶቻችሁን ለማጠናከር እና የሴቶች መረዳጃ ማህበርን የህይወታችሁ ተሳታፊ ክፍል እንዲሆን እንዲረዳችሁ ጥያቄዎቹን ተጠቀሙባቸው። ለተጨማሪ መረጃ ወደ www.reliefsociety.lds.org ሂዱ።***

**ስለጸጸት**

ፕሬዘደንት ሞንሰን፣ እንወድዎታለን። አዲሶችን ቤተመቅደሶች ስለመገንባት እና ስለወንጌል ሰባኪነት አገልግሎት ስላደረጉት በመንፈስ የተመራና ታሪካዊ ማስታወቂያ እና መሰግንዎታለን። በእነዚህም ምክንያት፣ ታላቅ በረከቶችን ወደ እኛና ወደፊት ትውልዶች እንደሚመጡልን እርግጠኛ ነኝ።

ውድ ወንድሞቼና እህቶቼ፣ ውድ ጓደኞቼ! ሁላችንም ሟች ነን። ይህ እንደማያስደነግጣ ችሁ ተስፋ አለኝ።

ማንኛችንም በምድር ላይ ለብዙ ጊዜ አንቆይም። በዘለአለማዊ አስተያየት አይንን ከመጨፈን በሚፈጥን አይነት ያጠረ ውድ የአመታት ቁጥሮች አሉን።

ከዚያም ከዚህ እንሄዳለን። መንፈሳችን “ህይወትን ወደ ሰጣቸው ወደ እግዚአብሔር” ይመለሳሉ።”[1] ወደ ሚቀጥለው አለም ስንሄድም ሰውነታችንን እና የዚህ አለም ነገሮችን ትተን እንሄዳለን።

በወጣትነታችን፣ ለዘለአለም የምንኖር ይመስለን ነበር። ከአድማስ አልፎ ያለ መጠን የሌለው የጸሀይ መውጣት አለ ብለን እናስብ ነበር፣ እናም ወደፊት ያለው ለዘለአለም ሳይሰበር የተዘረጋ መንገድ ይመስለን ነበር።

ነገር ግን፣ በእድሜ ስንገፋ፣ ወደኋላ እንመለከታለን እናም ያም መንገድ እንዴት አጭር እንደነበር እንገረማለን። አመታት እንዴት በፍጥነት እንዳለፉም እንደነቃለን። እናም ስለመረጥናቸውና ስላደረግናቸው ነገሮችም ማሰብ እንጀምራለን። በዚህም፣ ለነፍሳችን እርካታ እና ለልባችን ደስታ የሚሰጡ አስደሳች ነገሮችን እናስታውሳለን። ነገር ግን ደግሞም የምንጸጸትባቸውንም፣ እንዲሁም ተመልሰን ለመቀየር የምንመኛቸውን ነገሮች፣ እናስታውሳለን።

ለመዳን የማይችልን በሽተኛ ሰው የምትን ከባከብ አንድ ነርስ በሽተኛዎቹ ከዚህ ህይወት ለማለፍ በሚዘጋጁበት ጊዜ የምትጠይቃቸው ቀላል ጥያቂ አለ ብላለች።

“ማንኛውም የምትጸጸቱበት ነገር አለ?” ብላ ትጠይቃለች።[2]

ወደ ህይወት መጨረሻ ጊዜ መቅረብ በአብዣኛው ጊዜ ለሀሳብ ግልጽነት ያመጣል እናም ጥልቅ አስተያየት እና የነገሮች ትክክለኛ ገጽታ ይሰጣል። እነዚህ ሰዎች ስለሚጸጸቱት ሲጠየቁ፣ ልባቸውን ይከፍታሉ። ሰአትን ወደ ኋላ ለመመለስ ቢችሉ ምን እንደሚቀይሩም ያስቡበታል።

ያሉትን ሳስብ፣ በህይወት ከተጠቀምንባቸው፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መሰረታዊ መርሆች የህይወት መመሪዎቻችንን እንዴት እንደሚነኩ በማወቅ ያስደንቁኛል።

ስለወንጌል መሰረታዊ መርሆች ሚስጥራዊ የሆነ ምንም ነገር የለም። በቅዱሳት መጻህፍት አጥንተናቸዋል፣ በሰንበት ትምህርትም ተወያይተናቸዋል፣ እናም ለብዙ ጊዜ ከመስበኪያም ስለእነርሱ ሰምተናል። እነዚህ መለኮታዊ የሆኑ መሰረታዊ መርሆች ያልተጣመሙና ግልጽ ናቸው፤ የሚያምሩ፣ በጣም ጥልቅ፣ እና ሀይለኛ ናቸው፤ እናም ወደፊት የሚኖረንን ጸጸት ለማስወገድ ይረዳናል።

**ከማፈቅራቸው ሰዎች ጋር ተጨማሪ ጊዜ ባሳልፍ ኖሮ**

ምናልባት ወደሞት የቀረቡ በሽተኛዎች ከሚጸጸቱባቸው ነገሮች መካከል ዋናው ከሚወዷቸው ሰዎች ጋር ብዙ ጊዜ አለማሳለፋቸው ነው።

ወንዶች በአብዛኛው ይህን ለቅሶ ይዘምራሉ፥ “አብዛኛውን ህይወታቸውን በስራ በማሳለፋቸው በጥልቅ ይጸጸታሉ።”[3] ብዙዎች ከቤተሰብና ከጓደኞች ጋር አብሮ የሚያሳልፉት ምርጥ ጊዜዎች አምልጠዋቸዋል። ለእነርሱ ታላቅ ትርጉም ካላቸው ጋር ለማሳደግ የሚችሉትን ጥልቅ ግንኙነት አጥተዋል።

በብዙ ጊዜ በስራ በጣም አንጠመድምን? እናም ለማለት በሚያሳዝን ሁኔታ፣ በስራ መጠመድን እንደ ክንውን ወይም ታላቅ የህይወት ምልክት እንደሆነ በማሰብ በስራ መጠመዳችንን እንደ ክብር ማዕረግ እንለብሰዋለን።

ይህ ነውን?

ጌታችንን እና ምሳሌአችንን ኢየሱስ ክርስቶስን እና እርሱ በጋለሊና በኢየሩሳሌም ህዝቦች መካከል የነበረውን አጭር ህይወት አስባለሁ። በስብሰባዎች መካከል ወይም የተዘረዘሩ በፍጥነት መከናወን ያለባቸውን ነገሮች ለማከናወን ብዙ ስራዎችን እየሰራ በአዕምሮዬ አይን ለማይት እሞክራለሁ።

ይህን ለማየት አልችልም።

በዚህ ምትክ ርህራሄ ያለው እና የሚያስብ የእግዚአብሔር ልጅ አላማ ያለው ህይወትን በየቀኑ ሲኖርበት አያለሁ። በአካባቢው ካሉት ጋር ሲሰራም፣ እነርሱም አስፈላጊ እንደሆኑና እንደሚያፈቅራቸው ተሰማቸው። የተገናኛቸውን ሰዎች መጠን የሌለው ዋጋ እንዳላቸው ያውቅ ነበር። ባረካቸው፣ አገለገላቸውም። ከፍ አደረጋቸው፣ ፈወሳቸውም። ውድ የሆነውን ጊዜውንም ሰጣቸው።

በጊዜአችን ከሌሎች ጋር ጊዜ እንደምናሳልፍ ለማስመሰል ቀላል ነው። በኮምፒውተር፣ በፊት አንዱንም ሳንመለከት ብዙ ሺህ ከሆኑ “ጓደኞቻችን” ጋር “ለመገናኘት” እንችላለን። ቲክኖሎጂ አስደናቂ ነገር ለመሆን ይችላል፣ እናም በምናፈቅራቸው አጠገብ ለመሆን በማንችልበት ጊዜ ይህም በጥቅም ላይ ይውላል። ባለቤቴ እና እኔ ከምንወዳቸው የቤተሰብ አባላቶቻችን ርቀን ነው የምንኖረው፤ ይህም እንዴት እንደሆነ ተረድተናል። ነገር ግን፣ ከቤተሰብ ወይም ጓደኞች ጋር የምንገናኘው የሚያስቁ ነገሮችን፣ ተራ የሆኑ ነገሮችን በኮምፒውተር በመላክ፣ ወይም የምንወዳቸውን በኢንተርኔት በሚገኙት በማስተሳሰር ስለሆነ፣ እንደ ግለሰብ እና እንደ ህብረተሰብ በትክክለኛው መንገድ ላይ ያለን አይመስለኝም። ለእንደዚህ አይነት ነገሮች ቦታም አለው፣ ነገር ግን በዚህ ላይ ስንት ጊዜ ለማሳለፍ ፈቃደኞች ነን? ለእኛ በእውነትም በጣም አስፈላጊ ለሆኑት እራሳችንን እና የግል ጊዜአችንን ካልሰጠን፣ አንድ ቀን ጸጸት ይኖረናል።

ከእነርሱ ጋር ትርጉም ያለው ጊዜ በማሳለፍ፣ ነገሮች አብረን በማድረግ፣ እና እንደ ሀብት የምናያቸው ትዝታዎችን በመፍጠር፣ የምናፈቅራቸውን ዋጋ እንስጣቸው።

**በችሎታዬ በነበረኝ ብኖር ምኞቴ ነበር**

ሌላ ሰዎች የሚጸጸቱበት ቢኖር እነርሱ መሆን የሚገባቸውን ወይም የሚችሉትን ለመሆን ባለማቻላቸው ነው። ያለፈውን ህይወታቸውን ሲመለከቱ፣ በችሎታቸው መጠን እንዳልኖሩ፣ ለመዝፈን የሚቻለው እንዳልተዘፈነ፣ ይገባቸዋል።

የምናገረው በሙያ ውጤታማነት መሰላል ላይ ስለመውጣት አይደለም። ያም መሰላ፣ በዚህ ምድር ላይ ምንም ያህል ከፍተኛ የሆነ ቢመስልም፣ በሚጠብቀን በታላቁ የዘለአለም ጉዞ እንደ አንድ እርምጃ ብቻ ነው።

ዝለዚህ ሳይሆን፣ የምናገረው እግዚአብሔር፣ የሰማይ አባታችን፣ ምን አይነት ሰው እንድንሆን ስለፈለገበት ነው።

ገጣሚው እንዳለው፣ “የክብር ዳመናዎች እየተከተሉን”[4] ከቅድመ ህይወት ወደ አለም መጣን።

የሰማይ አባታችን እውነተኛ ችሎታችንን ያያል። እራሳችን የማናውቃቸውን ነገሮች እርሱም ስለእኛ ያውቃል። በህይወታችን ውስጥ የተፈጠርንበትን እንድናከናውን፣ መልካም ህይወት እንዲኖረን፣ እና ወደ እርሱ ፊት እንድንመለስ ያነሳሳናል።

አብዛኛውን ጊዜአችንን እና ጉልበታችንን ወዲያው በሚጠፋው፣ ምንም ጥቅም በሌለው፣ እና ጥልቀት በሌለው ላይ ለምን እናሳልፋለን? ተራ የሆነውንና ወዲያው የሚያልፈውን በመከተል ያለውን ጥፋት ለማየት እምቢ እንላለን?

“ብልም ዝገትም በማያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በማይሠርቁት ዘንድ ለእኛ በሰማይ መዝገብ [መሰብሰባችን]”[5] ጥበባዊ የሆነ አይደለምን?

ይህን እንዴት እናደርጋለን? የአዳኙን ምሳሌ በመከተል፣ ያስተማረውን በህይወታችን በመጠቀም፣ እግዚአብሔርን እና ሰዎችን በእውነትም በማፍቀር ነው።

ወደ ደቀ መዝሙርትነት ስንቀርብም እግሮቻችንን በማዘግየት፣ ሰዓታችንን በመመልከት፣ ወይም ስንሰራ ቅሬታን በማሳይት በእርግጠኝነት ይህን ማድረግ አንችልም።

በወንጌሉ ስለመኖር በተመለከተ፣ ጣቱን በውሀ ውስጥ አስገብቶ ለመዋኘት ሄጂ ነበር እንዳለው ልጅ መሆን አይገባንም። እንደ ሰማይ አባታችን ልጆች፣ ከዚህ በላይ የመሆን ችሎታ አለን። ለዚያም መልካም ማሰብ ብቻ ብቂ አይደለም። ማድረግአለብን። ከዚህም በጣም አስፈላጊ በሚሆን ሁኔታ፣ የሰማይ አባት እንድንሆን እንደሚፈልገን መሆን አለብን።

የወንጌል ምስክራችንን ማወጀችን መልካም ነው፣ ነገር ግን በዳግም ለተመለሰው ወንጌል ህያው ምሳሌ መሆን ግን የሚሻል ነው። ቃል ኪዳን ለገባናቸው ታማኝ ለመሆን መመኘት ጥሩ ነው፤ ምግባረ ጥሩ የሆነ ህይወት መኖር፣ አስራቶችንና ምጽዋቶችን መስጠት፣ የጥበብ ቃላትን ማክበር፣ እና እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን መርዳት የሆኑትን በማድረግ ለገባናቸው ቅዱስ ቃል ኪዳን ታማኝ መሆን ከዚህ በጣም የሚሻል ነው። ለቤተሰብ ጸሎት፣ ቅዱሳት መጻህፍትን ለማጥናት፣ እና ለመልካም የቤተሰብ መሳተፊያዎች ጊዜ እናስቀምጣለን ማለት ጥሩ ነው፤ ነገር ግን እነዚህ ነገሮች በሙሉ ማድረግ የሰማይ በረከቶችን ወደ ህይወታችን ሁልጊዜም ያመጧቸዋል።

ደቀ መዝሙርትነት ቅድስናን እና ደስታን መከተል ነው። ለራሳችን መሻሻል እና ደስታ የሚመራ መንገድ ነው።

አዳኙን ለመከተል እና እንድንሆን የታቀደክን አይነት ሰው ለመሆን በትጋት እንስራ። የመንፈስን መነሳሻ አድምጠን እንከተል። ይህን ስናደርግም፣ የሰማይ አባት ከዚህ በፊት ስለራሳችን የማናውቃቸውን ነገሮች ይገልጽልናል። ወደፊት ያለውን መንገድ ያበራልናል እናም የማናውቃቸውን እና ምናልባት የማናልማቸውን ችሎታችንን እንድናይ አይኖቻችንን ይከፍትልናል።

እራሳችንን ቅድስናን እና ደስታን በመፈለግ መለኮታዊ ስንሆን፣ በጸጸት መንገድ ላይ የመሆናችን ሁኔታ ይቀንሳል። በአዳኝ ጸጋ ላይ በተጨማሪ ከተደገፍን፣ የሰማይ አባት በእኛ ላይ ባለመው መንገድ ላይ እንደሆንን በተጨማሪም ይሰማናል።

**ራሴን ደስተኛ እንድሆን ብፈቅድ ምኞቴ ነበር።**

እንደሚሞቱ የሚያውቁት የሚጸጸቱበት ሌላው ነገር የሚያስደንቅ ነው። እነርሱም ራሳቸውን ደስተኛ እንዲሆኑ እንዲፈቅዱ ምኞት አላቸው።

በአብዛኛው ጊዜ መልካም የሆነ የቤተሰብ ሁኔታ፣ መልካም የሆነ የገንዘብ ሁኔታ፣ ወይም ለፈተና መጨረሻ የሚሆኑ አይነት ደስታ የሚያመጣልን ከምናገኘው አልፎ የሚገኝ አንድ ነገር እንዳለ እናልማለን።

ስናረጅም፣ ምንም ጥቅም የሌለውን ወይም ደስታችንን ለመወሰን የማይችለውን የውጪ ጉዳይ ወደኋላ እንመለከታለን።

እኛም ጥቅም አለን።እኛም ደስታችንን እንወስናለን።

እናንተና እኔ በደስታችን ላይ የመጨረሻ ሀላፊነት ያለን ነን።

ባልቤቴ፣ ሄሪየት፣ እና እኔ ቢስክሌትን መንዳት እንወዳለን። የፍጥረትን ውብት በመውጣት መመልከት አስደናቂ ነው። በቢስክሌት የምንጓዝባቸው መንገዶች አሉ፣ ነገር ግን ለምን ያህል እንደምንጓዝና በምን ፍጥነት እንደምንሄድ ከሌሎች ሰዎች ጋር በማመዛዘን አንመለከታቸውም።

ነገር ግን፣ አንዳንዴ መፎካከር የሚገባን ይመስለኛል። ራሳችንን ትንሽ ከፍ ባለ ሀይል እንድንሰራ ብናደርግ በጥሩ ሰዓት ለመድረስ ወይም በፍጥነት ለመጓዝ እንደምንችል አስብበታለሁ። እናም አንዳንዴም ለውዱ ባለቤቴ ይህን የመጥቀስ ትልቅ ስህተትንም እሰራለሁ።

እንደዚህ አይነት ለሆነ ሀሳብ ለማቀርበው መልሷም በጣም ደግ፣ ግልጽ፣ እና ቀጥተኛ ነው። ፈገግ ብላ፣ “ዲየትር፣ ይህ ፉክክር አይደለም፤ ይህ ጉዞ ነው። ጊዜውን ተደሰትበት” ትለኛለች።

እንዴት ትክክል ነች!

አንዳንዴ በህይወት ውስጥ በምንጨርስበት መስመር ላይ አተኩረን በጉዞው ደስታን አናገኝም። ከባለቤቴ ጋር በቢስክሌት የምጓዘው መጨረስን ስለምደሰትበት አይደለም። የምሄደው ከእርሷ ጋር ያለኝ አጋጣሚ አስደሳች ስለሆነ ነው።

የሚያልቁበትን ጊዜ በጉጉት በመጠበቅ አስደሳች አጋጣሚዎችን ማበላሸቱ ሞኝነት አይመስልምን?

አስደሳች ሙዚቃን ስንሰማ በዚህ ለመደሰት የመጨረሻው ድምጹ እስከሚጠፋ ድረስ እንጠብቃለን? አንጠብቅም። እናዳምጣለን እናም የተለያዩ ጣእመ ዜማ እና የሙዚቃ ምት ተስማምተው እንዲገኙ እናደርጋለን።

ጸሎታችንን “አሜን” በማለት ብቻ ወይም ስለመጨረሻው ብቻ በማሰብ እንጸልያለን? አንጸልይም። የምንጸልየው ከሰማይ አባት ጋር

ለመቀራረብ፣ መንፈሱን ለመቀበል፣
እና ፍቅሩ እንዲሰማን ለማድረግ ነው።

ደስታ ሁልጊዜ እንደሚገኝ በማወቅ
እንዳንደንግጥ፣ የወደፊት ጊዜ እስከሚመጣ
ድረስ ደስተኛ ለመሆን መጠበቅ አይገባንም።
ህይወት ወደኋላ በመመልከት እንድንደሰ
ትበት የሚሆን አይደለም። ዘማሪው እንደ
ጻፈው፣ "እግዚአብሔር የሠራት ቀን ይህች
ናት፤ ሐሤትን እናድርግ፥ በእርስዋም ደስ
ይበለን።"[6]

ወንድሞችና እህቶች፣ ጉዳያችን ምንም
ቢሆን፣ የምንታገልባቸው ወይም ፈተናዎ
ቻችን ምንም ቢሆኑ፣ በየቀኑ የምናቅፈውና
የምንወደው አንድ ነገር አለ። በየቀኑም
ከተመለከትንና ካደነቅን ምስጋናን እና ደስታን
የሚያመጣልን አንድ ነገር አለ።

ምናልባት በተጨማሪ በልባችን በመመል
ከት በአይናችን መመልከትን መቀነስ ይገባን
ይሆናል። "በልብህ ብቻ በግልጽ ተመልከት።
አስፈላጊ የሆነ ማንኛውን ለገር በአይን አይ
ታይም"[7] የሚለውን ይህን ጥቅስ እወደዋለሁ፥

"በሁሉም ነገሮች ምስጋና" እንድንሰጥ
ታዝዘናል።[8] ስለዚህ ያለንበትን መጥፎ ጉዳይን
ከማጉላት ይልቅ ምስጋና ሊኖረን የምንችለ
ውን ትትንሽ ነገሮች በአይንቻችንና በልባን
መመልከቱ አይሻልምን?

ጌታ ቃል እንደገባም፣ "ሁሉንም ነገሮች
በምስጋና የሚቀበል እርሱ የከበረ ይሆ
ናል፤ እናም የምድር ነገሮችም፣ እንዲሁም
በመቶ እጥፍ፣ አዎን በብዙ፣ ለእርሱ
ይጨመሩለታልና።"[9]

ወንድሞችና እህቶች፣ ከሰማይ አባታችን
ብዙ በረከቶች፣ ከደጉ የደህንነት አላማው፣
በዳግም ከተመለሰው ወንጌል፣ እና በዚህ ስጋዊ
የህይወት ጉዞ ውስጥ ከሚገኙ የሚያምሩ ነገ
ሮች ጋር "ለመደሰት ምክንያት የለንምን?"[10]

ጉዳዮቻችን ምንም ቢሆኑም፣ ደስተኛ
እንድንሆን የልብ ውሳኔ ይኑረን።

ስለውሳኔዎች

አንድ ቀን ከዚህ ስጋዊ ህይወት ወደሚቀ
ጥለው ህይወት ልናመልጠው የማንችለውን
እርምጃ እንወስዳለን። አንድ ቀን ስለህይወ
ታችን ወደኋላ ተመልክተን የተሻለ ለመሆን
እንደምንችል፣ የተሻለ ውሳኔ ለማድረግ
እንደቻልን፣ ወይም ጊዜአችንን በጥበብ
እንደተጠቀምን እናስብበት ይሆናል።

የህይወትን ጥልቅ ጸጸት ለማስወገድ ዛሬ
አንዳንድ ውሳኔዎችን ማድረግ ጥበባዊ ነው።
ስለዚህ፣ እነዚህ እናድርግ፥

- ከምናፈቅራቸው ጋር ብዙ ጊዜ ለማሳለፍ
  እንወስን።
- እግዚአብሔር እንድንሆን የፈለገን አይነት
  ሰው ለመሆን በጣም እንወስን።
- ሁኔታዎች ምንም ቢሆኑም ደስታን ለማግ
  ኘት እንወስን።

የነገዎቹ ጥልቅ ጸጸቶች ዛሬ አዳኝን
በመከተል ለማስወገድ እንደሚቻሉ እመሰ
ክራለሁ።፡ ኃጢያት ከሰራን ወይም ስህተት
ካደረገን፣ አሁን የምንጸጸትበት ምርጫዎችን
ካደረግን፣ ምህረት ለማግኘት የምንችልበት
ውድ የሆነው የክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ አለ።
ወደኋላ ለመመለስና የተደረገውን ለመቀየር
አንችልም፣ ነገር ግን ንስሀ ለመግባት እንች
ላለን። አዳኝ የጸጸት እምባችንን ለመጥረግ[11]
እና የኃጢያትን ሸክም ለማውረድ ይችላል።[12]
የኃጢያት ክፍያው ያለፈው እንድንተው እና
በንጹህ እጆች፣ በንጹህ ልብ፣[13] እና የተሻለ
ለማድረግና የተሻለ ለመሆን በመወሰን ወደፊት
እንድንሄድ ይፈቅድልናል።

አዎን፣ ይህ ህይወት በፍጥነት ያልፋል፤
ቀኖቻችን በፍጥነት የሚጠፉ ይመስላሉ፤
እና አንዳንዴም ሞት የሚያስፈራ ይመስላል።
ይህም ቢሆን፣ መንፈሳችን ለመኖር ይቀጥላል
እናም አንድ ቀን የዘለአለም ክብርን ለመቀበል
ከሞት ከተነሳው ሰውነታችን ጋር ይገናኛል።
በመሀሪው ክርስቶስ ምክንያት ሁላችንም
እንደገና እና ለዘለአለም ለመኖር እንደምንችል
እመሰክራለሁ። በአዳኛችን እና በቤዛችን ምክ
ንያት፣ አንድ ቀን "የሞት መውጊያ በክርስቶስ
ተውጧል"[14] የሚለው ትርጉሙ ምን እንደሆነ
በእውነት ገብቶን እንደሰትበታለን።

እንደ እግዚአብሔር ልጆች መለኮታዊ እጣ
ፈንታችንን የምናሟላበት መንገድ አንድና
ዘለአለማዊ ነው። ውድ ወንድሞቼና እህቶቼ፣
ውድ ጓደኞቼ፣ ይህን ዘለአለማዊ መንገድ
ዛሬመጓዝ አለባችሁ፤ አንድንም ቀን በቸል
ተኝነት ለመመልከት አንችልም። በእውነት
ለመኖር ለመሞት እስከምንደርስ ድረስ
እንዳንጠብቅ ጸሎቴ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ
ቅዱስ ስም፣ አሜን።

**ማስታወሻዎች**

1. አልማ 40፥11።
2. See Susie Steiner, "Top Five Regrets of the Dying," *Guardian*, Feb. 1, 2012, www.guardian.co.uk/lifeandstyle/2012/feb/01/top-five-regrets-of-the-dying.
3. Bronnie Ware, in Steiner, "Top Five Regrets of the Dying."
4. "Ode: Intimations of Immortality from Recollections of Early Childhood," *The Complete Poetical Works of William Wordsworth* (1924), 359.
5. ማቴዎስ 6፥20።
6. መዝሙር 118፥24።
7. Antoine de Saint-Exupéry, *The Little Prince*, trans. Richard Howard (2000), 63.
8. ሞዛያ 26፥39፤ ደግሞም ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 59፥7 ተመልከቱ።
9. ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 78፥19።
10. አልማ 26፥35።
11. ራዕይ 7፥17 ተመልከቱ።
12. ማቴዎስ 11፥28–30 ተመልከቱ።
13. መዝሙር 24፥4ተመልከቱ።
14. ሞዛያ 16፥8፣ ደግሞም 1 ቆሮንቶስ 15፥54 ተመልከቱ።

© 2012 በIntellectual Reserve, Inc መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩ.ኤስ.ኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፧ 6/11 (እ.ኤ.አ) ትርጉም የተፈቀደበት፧ 6/11 (እ.ኤ.አ) *Visiting Teaching Message, November* 2012 (እ.ኤ.አ) ትርጉም Amharic። 10371 506